✞ በወንድሞቹ ቂም አልያዘም / ዘፍ. 50÷15-22/

✞ ከእስራኤል ነገዶች የሁለቱ አባት ሆነ:: ያዕቆብም ብኩርናውን ለዮሴፍ ይሁን በማለት የዮሴፍን ልጆች ባረከ:: በስሞቻቸው ነገደ ኤፍሬምና ነገደ ምናሴ ተብለው ተጠሩ::ዘፍ.48፣ 2ኛ ዜና 5÷1፣ ዘኁ.1÷49፣ ዘዳ.33÷15-17::

ማጠቃለያ፡- በዘመነ አበው የነበሩ 22ቱ አበው የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. አዳም | 7. ሄኖክ | 13. ሳላ | 19. ታራ |
| 2. ሴት | 8. ማቱሳለ | 14. ዔቦር | 20. አብርሃም |
| 3. ሄኖስ | 9. ላሜሕ | 15. ፋሌቅ | 21. ይስሐቅ |
| 4. ቃይናን | 10. ኖኅ | 16. ረግው | 22. ያዕቆብ /1ኛ ዜና. 1÷1-27/ |
| 5. መላልኤል | 11. ሴም | 17. ሴሮሕ | |
| 6. ያሬድ | 12. አርፋክሳድ | 18. ናኮር | |

## ምዕራፍ ሁለት

## ዘመነ መሳፍንት

መስፍን ማለት ገዢ ወይም ዳኛ ማለት ነው:: በእስራኤል ነገሥታት ማስተዳደር ከመጀመራቸው በፊት ሀገሪቱን ከጠላት ወራሪ የሚያድን፣ የንጉሥ ዘር የሌለው ሰው ነው:: በተለይም ቤተ እስራኤል ወደ ሀገራቸው ከገቡና ኢያሱ ከሞተ በኋላ እግዚአብሔርን ትተው የአሕዛብን አማልክት በማምለክ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ እየሠሩ እግዚአብሔርን ያስቆጡት ነበር:: እርሱም ሊመልሳቸው ብሎ ለሚማርኳቸው ወራሪዎች አሳልፎ ይሰጣቸው ነበር:: ወራሪ በመጣ ቁጥርም እስራኤል ተጨንቀው ተጸጽተው ወደ እግዚአብሔር ይጮሁ ይጸልዩ ነበር:: እርሱም ይመራቸውና መሳፍንት እያስነሳ ከሚማርኳቸው እጅ ያድናቸው ነበር:: እስራኤልን መሳፍንት ያስተዳድሩበት የነበረው ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ከ1644 እስከ 1083 ዓመት /ከ3856-4417 ዓ.ዓ./ ያለው ጊዜ ዘመነ መሳፍንት ይባላል:: በመሳፍንት ግን የተዳኙት ለ450 ዘመን ነበር:: የሐዋ. 13÷20

**በዚህም ዘመን እስራኤልን ያስተዳደሩ 17 መሳፍንት ነበሩ::**

| | |
|---|---|
| 1. ሙሴ | 10. ኢያዕር /መሳ. 10÷3-5/ |
| 2. ኢያሱ | 11. ዮፍታሔ /መሳ. 1÷11/ |
| 3. ጎቶንያል /መሳ. 3÷12-30/ | 12. ኢብፃን /መሳ. 12÷8-10/ |

4. ናዖድ /መሳ. 3÷12-30/
5. ሰሜጋር /መሳ. 3÷31/
6. ቶላ /መሳ. 10÷1-2
7. ጌዴዎን /መሳ. 6÷8/
8. አቤሜሌክ /መሳ. 9÷1-57/
9. ነቢይት ዲቦራና ባርቅ /መሳ. 4÷1-24/
13. ኤሎም /መሳ. 12÷8-10/
14. አብዶን /መሳ. 12÷13-15/
15. ሶምሶን /መሳ. 13÷16/
16. ኤሊ /1ኛ ሳሙ. 4÷18/
17. ሳሙኤል /1ኛ ሳሙ. 7÷15/

**1. <u>ሙሴ</u>:-** ሕግ ለሕዝበ እስራኤል እንደ ጭራ ቀጥኖ በነበረበትና ወንዶች ልጆች እንዲገደሉ በተወሰነበት በዚያን ዘመን ሙሴ ከአባቱ እንበረምና ከእናቱ ዮካብድ ተወለደ:: ዘጸ.1÷20:: ሙሴ ማለት ከውኃ የተገኘ ማለት ነው::

- ✞ ልደቱና ዕድገቱ /ዘጸ.2÷1-11/
- ✞ ለዘሩ ተቆርቋሪነቱ /ዘጸ.2÷11-15/
- ✞ ወደ ምድያም መሰደዱ /ዘጸ. 2÷15/
- ✞ እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ እንዲያወጣ እንዳዘዘው /ዘጸ. 3÷10/
- ✞ ይረዳው ዘንድ ወንድሙ አሮን ከእግዚአብሔር ዘንድእንደ.ታዘዘ /ዘጸ.4÷10-17/
- ✞ ከአሮን ጋር ወደ ፈርኦን መግባታቸው /ዘጸ. 5÷1/
- ✞ ፈርኦንም «እግዚአብሔር አምላካችሁን አላውቅም፣ እስራኤል ባሮቼንም አልለቅም» በማለቱ የደረሱ አሥሩ መቅሠፍታት::
    1. የውኃ ወደ ደም መለወጥ /ዘጸ. 7÷20-25/
    2. ጓጉንቸር /ዘጸ.8÷6-15/
    3. ቅማል /ዘጸ. 8÷16-19/
    4. የዝንብ መንጋ /ዘጸ. 8÷20-30/
    5. ቸነፈር /ዘጸ. 9÷13-15/
    6. ሻህኝ የሚያመጣ ቁስል /ዘጸ. 9÷8-12/
    7. ነጎድጓድና በረዶ /ዘጸ. 9÷13-35/
    8. የአንበጣ መንጋ /ዘጸ.10÷1-20/
    9. ጨለማ /ዘጸ. 10÷21-29/
    10. የበኵር ልጅ ሞት /ዘጸ.17÷29-36/

እስራኤል ከግብጽ ወጥተው 40 ዓመት በምድረ በዳ ከተጓዙ በኋላ ወደ ተስፋቸው ሀገር /ምድረ ርስት/ ከመግባታቸው በፊት ሙሴ ሞተ/ ዘኍ.20÷1-23፣ መዝ.105÷32-33፣ ዘዳ.34/:: ከግብጽ ከወጡት ከ20 ዓመት በላይ የሆናቸው ከስድስት መቶ ሺህ እስራኤላውያን ውስጥ ከነዓን የገቡት ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ:: ዘዳ. 12÷37::

- ሙሴ የጌታ ምሳሌ ነው።

እስራኤል ከግብጽ የወጡት አራት ነገሮችን ስለጠበቁ ነው ሕዝ 16፥12

- ግዝረታቸውን ስላልተው
- ቋንቋቸውን ስላላጠፉ
- ስማቸውን ስላልለወጡና
- ምሥጢረ ተስፋቸውን ስላልገለጡ።

የዋሁ ሙሴ በአርአያነት ከሚታወቅባቸው የሕይወት ጉዞ ጥቂቶቹን እንመልከት፡፡

1. መፍቀሬ ሢመት አልነበረም።
2. በኀያልነቱ እጁን ብቻ በመዘርጋቱ ጠላቶቹን ድል ይመታ ነበር።
3. በጸሎቱ ተሰሚነት በአማላጅነቱ ብቃት፤
4. ለፈጣሪው በታማኝ አገልጋይነቱ፤
5. በጽዋሚነቱ
6. ከፈጣሪው እጅ በእጅ የሕግ ጽላት በመቀበሉ ይታወቃል።

2. **ኢያሱ፡-**

- ኢያሱ ማለት አዳኝ፣ መድኃኒት ማለት ነው።
- ከሙሴ ሞት በኋላ እስራኤልን መርቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከነዓን አስገብቷቸዋል። ምድሪቱንም አከፋፈላቸው። /መጽሐፈ ኢያሱ/
- ኢያሱ የጌታ ምሳሌ ነው።
- 110 ዓመት ሲሆነው ሞተ። /ኢያሱ 24፥29-31

## ጌልጌላ

- የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ባርነት ኑሮ ወጥተው ግዝረት የፈፀሙባት ሥፍራ ናት ጌልጌላ። ኢያሱ 5፥2-9
- እስራኤላውያን ወደ ምድረ ርስት ከመግባታቸው በፊት አላስፈላጊ የሆነ/ ሸለፈታቸውን/ ማስወገድ ነበረባቸውና በኢያሱ ምክንያት ይህን ሥርዓት በጌልጌላ ፈጽመዋል። ጌልጌላ ማለት አበሳ ማስወገጃ ቦታ ማለት ነው። የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። በብሉይ ኪዳን ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነውና ዛሬ ጥምቀትን በጌልጌላ ቤተክርስቲያን እንፈጽማለን። ኢያሱ የካህናት ምሣሌ ነው። ይህም ጥምቀት በካህናት አማካኝነት የሚፈጸምልን ምሥጢር እንደሆነ ያስረዳል።
- ዛሬ የእኛ ጌልጌላ (ቤተክርስቲያን) ለእኛ ለእስራኤል ዘነፍስ የሀዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ኃጢአት አበሳችን ሁሉ የሚወገድባት ቅድስት ሥፍራ ነች። በኃጢአት የተዳደፉ ንስሐ ገብተው አበሳቸው የሚርቅላቸው ወደ ቤተክርስቲያን ሲቀርቡ ነው።

- ስለሆነም ዛሬ ከህይወታችን ጋር ተጸናውቶን ያለውን አላስፈላጊ የኃጢአት ሸለፈት በቤተክርስቲያን ተገኝተን በቃሉ ሠይፍነት ቆርጠን ልናስወግደው ይገባል፡፡
- በሌላም በኩል እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ አሥራ ሁለቱ ድንጋዮች የመታሰቢያ ሐውልት ያቆሙት በዚሁ በጌልጌላ ነበር ኢያ 4፥19-20 ይህን ሀውልት ያቆሙት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ፍቅር ለማጽናት ያደረጉት የቃልኪዳን መግለጫ ነበር፡፡ ዛሬም በጌልጌላ ከምትመሰለው ቤተክርስቲያን ተሰብስበን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ፍቅር በምስጋና፣ በጸሎት፣ በዕንባ፣ በውዳሴ በዝማሬ፣ ንስሐ በመግባት፣ ሥጋ ወደሙን በመቀበል ልንገልጽ ያስፈልጋል፡፡ የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር አበሳችን ሁሉ በሚርቅባት በቅድስት ቤተክርስቲያን እንዲያጸናን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን፡፡

3. **ጌዲዎን፡-**

- እስራኤላውያንን ከምድያማውያን ሊያድን ተጠራ፡፡ /መሳ. 6፥11-24/
- የበዓልን መሠዊያ ካፈረሰ በኋላ ይሩበዓል ተብሎ ተጠራ፡፡ /መሳ. 6፥25-32/
- 32000 ሰዎች ሲወጡለት በእግዚአብሔር ትዕዛዝ 300 ሰዎችን አስከትሎ ምድያማውያንን በማባረር አሸነፋቸው፡፡ /መሳ. 6፥32፣ 8፥21/
- የጌድዮን ፀምር የእመቤታችን ምሳሌ ነው፡፡ /መሳ. 6፥37-40/
- ሕዝቡ «በእስራኤል ላይ ንገሥ» ቢሉት እምቢ ብሎ 40 ዓመት ፈራጅ ሆነ፡፡ /መሳ. 8፥22-23/
- እምነቱ በዕብ. 11፥32 ተመስክሮለታል፡፡

4. **ዮፍታሔ**

- ከእስራኤል መሳፍንት አንዱ ሲሆን የአንዲት ጋለሞታ ሴት ልጅ ነበረ፡፡ መሳ. 11፥1
- ከሌላ የሚወለዱ የአባቱ ልጆች ከአደጉ በኋላ ከእኛ ወገን አይደለህም ርስት መውረስ አይገባህም ብለው አባረሩት፡፡ እሱም ሰባ ከሚሆኑ ተከታዮቹ ጋር ሸሽቶ በእናቱ አገር በጦብ ምድር ተቀመጠ፡፡ መሳ. 11፥2-3
- አሞናውያን በእስራኤል ላይ በዘመተባቸው ጊዜ እስራኤላውያን በእኛ ላይ አለቃ ሆነህ ጠላቶቻችንን አጥፋልን አሉት፡፡ በእምነት አሞናውያንን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል መትቶ አሸናፋቸው፡፡ መሳ. 11፥6-21፣ ዕብ. 11፥32

* አሞናውያን በእስራኤል ላይ በዘመቱባቸው ጊዜ እስራኤላውያን በእኛ ላይ አለቃ ሆነህ ጠላቶቻችንን አጥፋልን አሉት፡፡ በእምነት አሞናውያን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል መጥቶ አሸነፋቸው፡፡ መሳ. 11፥6-21 ዕብ 11፥32
* ዮፍታሔ ጠላቶቹን ድል ነስቼ በደህና የተመለስሁ እንደሆነ በመጀመሪያ ከቤቱ ደጅ ወጥቶ የሚቀበለኝን ማንኛውንም እሠዋለሁ ብሎ ተሳለና ዘመተ፡፡ አሞናውያንን ድል አድርጎ ሲመለስ ልጁ ልትቀበለው ወጣች፡፡ በስዕለቱ መሠረት የሚወዳትን ሴት ልጁን ሰዋ፡፡ መሳ. 11÷34-39
* ስድስት ዓመት በእስራኤል ላይ ፈራጅ (አስተዳዳሪ) ሆነ፡፡

**ጥያቄ**

1. ከዮፍታሔ ታሪክ ምን እንማራለን?

**5. ሶምሶን፡-**

* የተወለደው በመልአክ ብሥራት ነው፡፡ /መሳ. 13÷2-23/
* 15 ዓመት ሲሆነው አባቱ ለጉዳይ ወደ ምድረ ኤሎፍሎ ይዞት ሄደ፡፡ በመንገድም የአንበሳ ደቦል አግኝቶ እንደ ጠቦት በእጁ ቆራረጠው፡፡ ከሄደበት ሲመለስ አንበሳ መደብ ለመቀመጥ፣ አውሬ ለመቀስቀስ፣ የገደለው አንበሳ እንዴት እንደሆነ ለማየት ሲሄድ የአንበሳው ሬሳ ውስጥ ንብ ሠፍሮበት ማርም ተሠርቶበት አገኘ፡፡ ከማሩም ቆርጦ በልቶ ለአባቱና ለእናቱም ይዞላቸው ሄደ፡፡ «ከበላተኛ ውስጥ መብል ወጣ፣ ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ» የተባለው በዚህ ጊዜ ነው፡፡ /መሳ.14÷5-15/
* ከፍልስጤማዊቷ ደሊላ ጋር በመወዳጀቱ የተሰጠውን ፀጋ አጥቷል፡፡ /መሳ. 16÷30/
* ሶምሶን የጌታ ምሳሌ ነው፡፡
* ሶምሶን በእስራኤል ላይ 20 ዓመት ፈረደ፡፡ /መሳ. 16÷31

**6. ዔሊ**

* ከአሮን ወገን የሆነና በሊቀ ካህንነትና በመሳፍንትነት እስራኤልን ያስተዳድር ነበር፡፡
* በእሱ ዘመን የእግዚአብሔር የመቅደሱ ድንኳን በሴሎ ተተክሎ ነበር፡፡ 1ኛ.ሳሙ. 19÷1 ልጆቹ አፍኒንና ፊንሐስ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተው በተገኙ ጊዜ እንደ ካህንነቱ ልጆቹን በሚገባ ስላልገሰጸ በደካማነቱ ተነቀፈ፡፡ 1ኛ.ሳሙ. 2÷11-36፣ ልጆቹን ባለመቅጣቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር የተገለጠለት ፍርድ ለዔሊ ተነገረው፡፡ 1ኛ ሳሙ. 3÷11-14

* እግዚአብሔርም የተናገረው ነገረ ተፈፀመ፡፡ ልጆቹ በጦር ሜዳ ላይ ሞቱ የእግዚአብሔርም ታቦት ተማረከች ዔሊም ይህን ሲሰማ ከድንጋጤው የተነሳ ወድቆ ሞተ፡፡ 1ኛ.ሳሙ. 4÷10-18 ካህናትም ከዔሊ ቤት ተወሰዱ ለሌላም ተሰጡ፡፡ 1ኛ ነገ. 2÷26-27

7. <u>ሳሙኤል</u>

* አባቱ ሕልቃና እናቱ ሐና ይባላሉ፡፡ 1ኛ.ሳሙ. 11
* ከሕፃንነቱ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ይገለጥለት ነበር፡፡ 1ኛ ሳሙ. 2÷18፣ 3÷1 ዔሊ ከሞተ በኋላ በእስራኤል ላይ ፈራጅና አገልጋይ ካህን ሆኖ ያስተዳድር ነበር፡፡ 1ኛ. ሳሙ. 10÷1፣7÷15-17 በእግዚአብሔር ትዕዛዝ በካህንነቱ ሳኦልንና ዳዊትን ቀብቶ አንግሷል፡፡ 1ኛ ሳሙ. 10÷1፣ 16÷1-13
* ሳሙኤል በአገሩ በአርማቴም ሞተና በቤቱ ተቀበረ፡፡ 1ኛ ሳሙ. 25÷1

## <u>ማጠቃለያ</u>:-

ዘመነ መሳፍንት ከሕገ ልቡና ዘመን ይልቅ ለአማናዊት ቤተ ክርስቲያን የቀረበ ነው:: ምክንያቱም:-

1. ሕገ ኦሪት የተሰጠበት በመሆኑ፣
2. ታቦተ ሕግ የተሰጠበት በመሆኑ፣
3. ደብተራ ኦሪት የተሠራችበት በመሆኑ፣ /ዘጸ. 26/
4. የበዓላት ቀኖና ስለተጀመረበት፣ /ዘጸ. 23/
5. ካህናት በሕግ የተሾሙበት ዘመን በመሆኑ፣ /ዘፍ. 28÷6/
6. በቤተክርስቲያን ዛሬ የምናገኛቸው ንዋየ ቅድሳት ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት መዋል የጀመሩበት ዘመን በመሆኑ:: /ዘጸ. 27÷3/

✞ በዘመነ መሳፍንት የነበሩ ለሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎች ከሆኑት መካከል

1. ደብተራ ኦሪት - ለቤተክርስቲያን ሕንፃ
2. ሌዋውያን ካህናት - ለሐዲስ ኪዳን ካህናት
3. የበግ መሥዋዕት - ለሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት
4. በዓላተ ኦሪት - ለቤተክርስቲያን በዓላት
5. ደብረ ሲና /ኮሬብ/ - ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበር::

# ምዕራፍ ሦስት
# ዘመነ ነገሥት

ሕዝበ እስራኤል የአካባቢያቸውን አሕዛብ ነገሥታት በማየት ካህኑ ሳሙኤልን ንጉሥ አንግሥልን ብለው ጠየቁት:: ሳኦልንም አነገሠላቸው:: ከሳኦል እስከ ይሁዳ መንግሥት ማለቂያ ነገሥታት ለ497 ዓመት ነግሠዋል:: /4417-4914 ዓ.ዓ/

**ሳኦል**:-

- ☞ ከብንያም ወገን የሚሆን የቂስ ልጅ ነው::
- ☞ ኃያል ከመሆኑ የተነሳ ሊዋጋ በሄደበት ሁሉ ድል ያደርግ ነበር:: 1ኛ ሳሙ. 14÷17
- ☞ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመጠበቁ እግዚአብሔር ናቀው፤ መንግሥቱንም ለየው:: 1ኛ ሳሙ. 15
- ☞ በሕይወት እያለ ዳዊት ተቀባ፤ ሳኦልንም የእግዚአብሔር መንፈስ ራቀው:: ክፉም መንፈስ ሲያሰቃየው ዳዊት በገና እየደረደረ ያርቅለት ነበር:: 1ኛ ሳሙ. 6÷12-23
- ☞ ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጋ ቀላፋን መጥተው እንዳይገድሉኝና እንዳይሳለቁብኝ ሲል እራሱ በሰይፉ ላይ ወድቆ በጊልቦአ ተራራ ሞተ:: 1ኛ ሳሙ. 31
- ☞ ሳኦል በእስራኤል ላይ ለ40 ዓመት ነገሠ:: የሐዋ. 13÷21

**ዳዊት**:-

- ☞ ከበግ እረኝነት የተጠራ ንጉሥ ነው:: 1ኛ ሳሙ. 16÷1-13
- ☞ ገና በአሥራ ሁለት ዓመቱ ይፈሩትና ይንቀጠቀጡለት የነበረውን ጎልያድን ድል አድርጎታል:: 1ሳሙ.7÷16::
- ☞ ሕዝበ እስራኤል ስለወደዱት ሳኦል ያሳድደው ነበር::
- ☞ ሳአል ከሞተ በኋላ ዳዊት መንገሥ ሲጀምር የ30 ዓመት ልጅ ነበር::
- ☞ ለእግዚአብሔር ታቦት ከፍተኛ ክብር ይሰጥ ነበር:: 2ኛ ሳሙ. 6÷23
- ☞ በኬብሮን፣ በይሁዳ ለ7 ዓመት ከስድስት ወር፣ በኢየሩሳሌም ፣ በእስራኤልና በይሁዳ ሁሉ ላይ 33 ዓመት በጠቅላላ 40 ዓመት ከነገሠ በኋላ ከአባቶቹ ጋር አንቀላፋ:: በዳዊት ከተማም ተቀበረ:: 1ኛ ነገ.2÷10-12::

- ☞ እግዚአብሔርን ቢበድልም በፀፀትና በንስሐ ተመለሰ:: 2ኛ ሳሙ. 12÷1-23
- ☞ ለዳዊት ሰባት ሀብታት ተሰጥተውት ነበር::
- ☞ የዳዊት መንግሥት የክርስቶስ መንግሥት ምሳሌ ነበር:: ኢሳ. 9÷7፣ ለቃስ 1÷32

**ሰሎሞን:-**

- ☞ የነገሠው ገና ብላቴና ሳለ ማስተዋል በማይችልበት ጊዜ ነው:: 1ኛ ነገ. 3÷7
- ☞ እግዚአብሔር ብዙ ማስተዋልና ጥበብ ሰጥቶት ነበር::1ኛ ነገ. 3÷16-25
- ☞ በዘመኑ የነበሩ ሕዝቦችና ነገሥታት ሁሉ ጥበቡን ለማየት ወደ አገሩ ይጎርፉ ነበር:: 1ኛ ነገ 10
- ☞ በንግሥተ ሳባ ማክዳ እና በልጇ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ታቦተ ጽዮንና ሕገ ኦሪት ወደ አገራችን ገባ::
- ☞ እግዚአብሔር አምላክ በዳዊት ዘመን እንዲሠራ ያልፈቀደውን ቤተ መቅደስ እንዲሠራ ፈቀደለት:: በመንፈስ ጀምሮ በሥጋ ጨረሰ፤ የእግዚአብሔር በረከት ራቀው፤ መንግሥቱም ይከፈል ዘንድ ምክንያት ሆነ:: በእስራኤል ላይ 40 ዓመት ነግሦ በዳዊት ከተማ አንቀላፋ፣ በዛም ተቀበረ:: 1ኛነገ.11÷40-43::

**ሮብዓም:-**

- ➢ ሮብዓምም ንጉሥ በሆነ ጊዜ የአርባ አንድ ዓመት ጎልማሳ ነበር:: ለ17 ዓመታት የይሁዳን መንግሥት አስተዳድሯል:: 1ኛ ነገ. 14÷21
- ➢ ሮብዓም እንደነገሠ አባቱ ሰሎሞን የጫነውን ቀንበር ያቀልላቸው ዘንድ፣ሕዝቡ ጠየቁት ካቀለለላቸው ለእርሱ እንደሚገዙለት፤ እስራኤላውያን ሮብዓምን ቢጠይቁት ከሦስት ቀናት በኋላ እንደሚመልስላቸው ቃል ገብቶ፤ ሽማግሌዎች የመከሩትን ምክር ትቶ ከእርሱ ጋር በፊቱ ይቆሙ ከነበሩት ብላቴኖች ጋር ተማክሮ እንዲያውም ጫናውን እንደሚያከብድባቸው ነገራቸው:: ይህና ሌሎች ምክንያቶች ሆነው እስራኤል /ምድረ ፍልስጥኤም፣ በ922 ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ለሁለት ተከፈለች:: 1ኛነገ. 12÷1-18:: በዚህ ጊዜ ሁለቱ ነገድ /ብንያምና ይሁዳ/፣ አሠፋፈራቸው በደቡብ ፍልስጥኤም ሲሆን ዋና ከተማቸው ኢየሩሳሌም፣ ንጉሣቸውም ሮብአም ነበር:: መንግሥታቸውም «የይሁዳ መንግሥት» ተባለ:: 1ኛነገ. 12÷25:: የተከፋፈለ ሕዝብ ለጠላቶች ጥቃት የተመቸ ነውና በ792 ከክርስቶስ ልደት በፊት ሰሜኑን ክፍል አሦራውያን በስምናሶር መሪነት ወግተው ማረኩ:: 1ኛ ነገ. 17:: በደቡብ የነበሩት እንደ

ጠላት ያዩአቸው ስለነበር ደስ ሳይላቸው አልቀረም:: በሰሜኑ የደረሰው ወረራ ለደቡብም አልቀረለትም:: በ586 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባቢሎናውያን በናቡከደነጾር መሪነት መጥተው ኢየሩሳሌምን አጠፉ:: ቤተመቅደስንም አፈረሱ፤ ሕዝቡንም ማርከው ወሰዱ::

## ማጠቃለያ

በዚህ ዘመን በደብተራ ኦሪት የነበረችው ታቦተ ጽዮን ወደ ቤተ መቅደስ ገባች:: እንዲሁም ዛሬ ላለው የቤተክርስቲያን አሠራር መሠረት የጣለ ዘመን ነበር:: ንጉሡ ዳዊትም በሰሞን የተመደቡ / ሰሞኛ ካህናት/ ካህናትና መዘምራንን፣ ሰሞነኞችን፣ ለቤተ መቅደስ በመመደብ ዛሬ ለምንጠቀምበት ሥርዓት መሠረቱን አስቀምጧል:: ሌላው ይህን ዘመን ልዩ የሚያደርገው በንጉሥ ሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ታቦተ ጽዮን ወደ ኢትዮጵያ መምጣቷ ነው::

እስራኤላውያን ለሁለት ከተከፈሉ በኋላ በይሁዳና በእስራኤል የነገሡ ነገሥታትና በዘመናቸው የነበሩ ነብያት እንዲሁም በጊዜው የነበሩ ሌሎች መንግሥታት የሚከተሉት ናቸው::

**በይሁዳና በእስራኤል የነገሡት ነገሥታትን በዘመኑ የነበሩት የነቢያት ዝርዝር ሰንጠረዡ በገጽ 258 ይመልከቱ**

## ምዕራፍ አራት

ይህ ዘመን የአይሁድ ንጉሥ ሴዴቅያስ በባቢሎን ምርኮ ከሞተ በኋላ /2ኛ ዜና. 36÷1-16/ ያለውን ጊዜ በተለይ ይመለከታል:: ይህም ከ586 ከክርስቶስ ልደት በፊት እስከ ክርስቶስ መወለድ ያለው ጊዜ ነው:: ይህም 4914-5500 ዓመተ ዓለም ነው::

***ነቢያት***:- በአጠቃላይ እውነተኞችና ሐሰተኞች ተብለው በሁለት ሲከፈሉ በቅዱሳት መጻሕፍት የምናገኛቸውና ከእውነተኛ አምላክ ከእግዚአብሔር የሆኑትን ነቢያት የቃል እና የጽሑፍ ብለን እንለያቸዋለን::

- የጽሑፍ ነቢያት በማዕረጋቸው /በብቃታቸው/ ዐበይትና ደቂቅ ይባላሉ::
- የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳን ነቢይ አዳም፤ የመጨረሻው መጥምቀ
- መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ፤ ሊቀ ነቢያት ደግሞ ነቢይና መስፍን የነበረው ሙሴ ነው::

***ካህናት***:- ክህነት ተክህነ፣ አገለገለ፣ ተሾመ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሹመት፣ አገልግሎት፣ በተቀበሉት ሥልጣን መሥራት ወይም አገልግሎት መፈጸም ይሆናል::